# ሚዲያ ለኢትዮጵያ የህዳሴ ጉዞ

ኢዛና ዘመንፈስ

09-10-17

ባለፈው ሰኞ ነሐሴ 22 ቀን እዚሁ መዲናችን አዲስ አበባ ውስጥ የተካሄደ አንድ ሚዲያ ነክ የምክክር መድረክ እንደነበር አስታውሳለሁ። የውይይቱ ዋነኛ ትኩረት በተለይም የግል መገናኛ ብዙኃን ተቋማትን ገንቢና ገንቢ ያልሆኑ ጎኖች የሚመለከት ግብረ መልስ ላይ የተመሰረተ ግምገማ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ይመስለኛል። እናም በዚያው መድረክ ላይ ተገኝተው የየራሳቸውን ሚዲያ ነክ አስተያየት የሰጡ የመንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች፤ እንዲሁም ደግሞ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡ ምሁራን ጭምር የጋራ መግባባት ያሻዋል የሚል ተመሳሳይ አንድምታ ያለውን አቋም ያንፀባረቁበት ሆኖ ስለተሰማኝ ቁልፍ ነጥብ ጥቂት ለማለት ነው እኔም የፈለግኩት።

በዚህ መሰረትም ሰሞነኛው ሚዲያ ነክ የምክክር መድረክ ላይ ተገኝተው የበኩላቸውን ጠቃሚ ሃሳብ ሲሰጡ ከሰማሁዋቸው የኢፌድሪ መንግስት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች መካከል አንዱ የነበሩት፤ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አባዱላ ገመዳ ከተናገሩት ውስጥ ጥቂት አንኳ አንኳር ነጥቦችን በማስታወስ እጀምር ዘንድ ጠቃሚ መስሎ ይሰማኛል። ምክንያቱም ደግሞ ክቡር አፈጉባኤው ነሀሴ 22 ቀን 2009 ዓ.ም በተካሄደውና በተለይም የግል መገናኛ ብዙኃንን ሚና የሚያስቃኝ ሃሳብ በተነሳበት መድረክ ላይ “ኒኩለርን ለበጎ ዓላማ እንጠቀምበት ብለው ያመኑ ሰዎች ህዝብን ለሚጠቅም የልማት ተግባር እንደሚያውሉት ሁሉ፤ በተቃራኒው ዓለማችንን ወደ ፍፁም የጋራ ጥፋት ለሚወስድ አደገኛ ተግባር ሊጠቀሙበት ሲሞክሩ የሚስተዋሉም ግን አሉ። በእኔ እምነት ሚዲያም ልክ እንደዚያው ነው ማለት ይቻላል” ሲሉ ጀምረው የሩዋንዳውን የዘር ማጥፋት ዕልቂት ስላልከተለው ምክንያት ያወሱበት ንግግር መዳበር የሚገባው ገዢ ነጥብ ሆኖ አግኝቸዋለሁና ነው።

ስለሆነም፤ ክቡር አቶ አባዱላ “መንግስት በአገራችን ዴሞክራሲ እንዲኖር ስለሚፈልግ ነው ለግል ሚዲያ መጠናከር የበኩሉን ጥረት እያደረገ የሚገኘው” ሲሉ ያከሉትንም ማብራራቱ ጠቃሚ ይመስለኛል። የሀገራችንን የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ሙያዊ ቁመና፤ የኃላፊነት ስሜት የተላበሰና ሚዲያ ልክ እንደ የኒዩክሌር ኃይል በያዥው ፍላጎት ሊወሰን የሚችል ድምር ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ወደ ተያይዞ መጥፋት አደጋ እንዳይወስደን ተገቢውን ጥንቃቄ እያደረግን፤ ልንጠቀምበት እንደሚገባ በጥልቀት የሚያስገነዝብ ነው የአቶ አባዱላ ገመዳ ገለፃ ማለቴ ነው።

ስለዚህ እኔ ራሴም ብሆን ከላይ ለአብነት ያህል በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ የተወሳውን የክቡር አፈጉባኤው ጠቃሚ ምክር ለማጠናከር ይረዳል የምለውን ተጨማሪ አስተያየት መሰንዘር እንዳለብኝ ያመንኩት ያለምክንያት አይደለም። ይልቅስ ላለፉት 25 ያህል ዓመታት ሀገራችን ውስጥ እየታተሙ ሲሰራጩ ስለምናውቃቸው አብዛኛዎቹ የግል ፕሬስ ሚዲያ ውጤቶች ሙያዊና ሥነ ምግባራዊ ቁመና ጉዳይ፤ አንስተን ለመነጋገር በሞከርን ቁጥር፤ ቀድሞ ወደ አእምሮአችን መምጣቱ የማይቀረው፤ የኢትዮጵያውያን ህዝቦችን

ፈርጀ ብዙ ብዝኃነት በአግባቡ የማስተናገድን አስፈላጊነት፤ አምኖ ካለመቀበል የሚመነጭ የሚመስል የኃላፊነት ስሜት ማጣት አሳሳቢ ችግር በጎላና በሰላ መልኩ የሚስተዋልባቸው እየሆኑብን የመቆየታቸው ነገር ስለሆነ እንጂ።

ጉዳዩን ክቡር የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ አባዱላ ገመዳ በሰሞነኛው ሚዲያ ነክ የውይይት መድረክ ላይ ባደረጉት ንግግር ከተገለፀበት አግባብ አኳያ ቃኝተን እንመልከተው ከተባለ፤ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ዓይነቶቹ ሀገራት ውስጥ ለሚኖሩ ህዝቦች ማንኛውም የመገናኛ ብዙኃን አውታር አስፈላጊ የሚሆነው፤ የኒኩሌር ኃይልን ለምጣኔ ሀብታዊ ዕድገትና ብልጽግና የማዋል ተግባር ሊጠይቅ የሚችለውን ያህል ጥንቃቄ ሲታከልበትም ጭምር ነው ብለን ብናጠቃልል ተጨባጩን ጥሬ ሀቅ በተሻለ መልኩ የሚያሳይልን ይመስለኛል። እናም ይህን በክቡር አፈ ጉባኤው ለባለድርሻ አካላት የተለገሰ ጠቃሚ ምክር ያዘለውን መሰረተ ሃሳብ ልብ ከማለት ሳንቦዝን፤ እርሳቸው በተጋባዥነት ተገኝተው ንግግር ባሰሙበት ሰሞነኛ ሚዲያ ነክ የውይይት መድረክ ላይ የታደሙ የሙያ ዘርፉ ልሂቃን በተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ከሰነዘሩት ተያያዥነት ያለው ሃሳብ መሀል እየቀነጨብን እንመልከት።

ስለዚህም ሌላው በእዚያ መድረክ ታዳሚዎች ዘንድ ሰፊ ውይይት እንደተካሔደበት የተረዳሁት ነጥብ፤ በተለይም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና የመገናኛ ብዙኃን ትምህርት ክፍል መምህሩ ዶክተር ተሻገር ሽፈራው፤ የሀገራችን የግል ሚዲያዎች ድክመትና ጥንካሬ ላይ የሚያጠነጥን ዳሰሳ ያቀረቡበትን ጥናታዊ ጽሑፍ ነው። የተሻገር ፅሑፍ ለሙያ ዘርፉ ካላቸው ቅርበት አኳያ ተቃኝቶ የቀረበ "አካዳሚያዊ" ትንተና ነው ብንልም ስህተት እንደማይሆን ይሰማኛል። እኔን ወደ እንደዚህ ዓይነት አስተያየት ያደረሰኝ ምክንያትም ጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢው ጋዜጠኝነትን ለረጅም ጊዜ ካስተማሩ የሀገራችን ጎልማሳ ምሁራን መካከል የሚመደቡ ከመሆናቸውም ባሻገር ፤ ጎበዝ የሚባሉ ገጣሚም ጭምር እንደሆኑ አውቃለሁና ነው። ለዚህም ይመስላል ተሻገር ሽፈራው ባቀረቡት ጥናታዊ ወረቀት (ፅሑፍ) ላይ ስለየግሉ ፕሬስ ሚዲያ ጋዜጠኞች መሰረታዊ ችግር ከመቸውም ጊዜ በተሻለ መልኩ ሊነግሩን መድፈራቸው።

ለአብነት ያህልም "የግሉ ፕሬስ ሚዲያዎች ዋነኛ ችግር ራሳቸውን እንደ አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል አድርገው ስለሚቆጥሩ ነው ማለት ይቻላል" የሚል ሃሳብ ሰንዝረዋል ዶክተር ተሻገር ሽፈራው። ከዚሁ የግሉ ፕሬስ ሚዲያ ጋዜጠኞች መሰረታዊ የአመለካከት ችግር የተነሳ፤ የመንግስትን ጥቃቅን ድክመቶች ሳይቀር እያጋነኑ በማስጮህ ሲያወግዙ ማየት የተለመደ ጉዳይ እንደሆነና በአንፃሩ ኢህአዴግ መራሹ መንግስት የሚነድፋቸው ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ለሀገራችን አጠቃላይ ገጽታ መለወጥ የማይናቅ በጎ ተጽእኖ የፈጠረ ውጤት ስለማምጣታቸው ጉዳይ ትንፍሽ የሚል የግሉ ፕሬስ ሚዲያ ማግኘት እንደብርቅ ሲቆጠር መቆየቱንም አክለው ገልፀዋል ጽሑፍ አቅራቢው ተሻገር ሽፈራው።

እንዲሁም ደግሞ አንድ ሌላ የምክክር መድረኩ ተሳታፊ ግለሰብ "የኛ አገር የግል ሚዲያ ጋዜጠኞች በእርግጥም ሙያዊ ኃላፊነት የሚሰማቸው ቢሆኑ ኖሮማ ሌላው ቢቀር የሙስና ችግር ህዝቡን እስከዚህ ድረስ ሲያስመርረው፤ እያዩና እየሰሙ ዝም አይሉም ነበር" ሲሉ የዶክተር ተሻገርን ሃሳብ የሚያጠናክር አስተያየት ሰጥጠዋል። አሁንም ቢሆን የግል ሚዲያዎችን መንግስት በጀመረው የፀረ ኪራይ

ሰብሳቢነት ትግል ውስጥ ተሰልፈው የየራሳቸውን ገንቢ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ እንደሚገባና ጊዜው ብዙም እንዳልረፈደ ነው አስተያየት ሰጪው ግለሰብ ያስገነዘቡት።

ያም ሆነ ይህ ግን የውይይት መድረኩ ላይ በታደሙት ወገኖች የተነሳው ሃሳብ ሲጠቃለል "ኢትዮጵያ ውስጥ ከፖለቲካዊ የአስተሳሰብ ወገንተኝነት በፀዳ ገለልተኝነት የሚሰራ የግል ሚዲያ ተቋም የለም" የሚል አንድምታው ይበልጥ የጎላ ሆኖ ነው ያገኘሁት እኔ በበኩሌ። ንብረትነታቸው የህዝቡ እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰደውና ግን ደግሞ በተለምዶ "የመንግስት" ተብለው የሚጠሩት የሀገራችን መገናኛ ብዙኃን "የለየላቸው የኢህአዴግ ልሳናት" መሆናቸውን የሚናገሩ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች የዚያኑ ያህል ናቸው ተብሎ እንደሚታመንም አልዘነጋሁትም።

እናም ከዚህ የሁለት ተቃራኒ ጽንፎች መገለጫ ወገንተኝነት አኳያ ሲታይ፤ እውን ኢትዮጵያ ውስጥ መካሄድ የሚኖርበትን ጤናማ መድበለ ፓርቲያዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ የተመሰረተ ሰላማዊ ትግል የሚያስተናግድ ነፃ ሚዲያ መፍጠር ይቻል ይሆን? ብለን ራሳችንን እንድንጠይቅ መገደዳችን አይቀርም። ምክንያቱም ደግሞ፤ ለሀገራችን የህልውና ጉዳይ ተደርጎ የሚወሰደውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የመገንባት ጥያቄ በሚያጠግብ ፍጥነት መመለስ ካለብን፤ በሒደቱ ላይ የተረጋገጡትን እንደ የመልካም አስተዳደር እጦትና የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ችግር የሚገለጽባቸው የፍትህ ርትዕ ማነቆዎችን ትርጉም ባለው መልኩ መቅረፍ ይጠበቅብናልና ነው።

ያን ለማድረግ ይቻል ዘንድም፤የሁሉም ችግሮቻችን የመፍትሔ ቁልፍ በማይናወጥ የሕግ የበላይነት ጥላ ስር የሚካሔድ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ነው የሚል ጽኑ አቋም ይዞ የተነሳ ሀገር አቀፋዊ ነፃ ሚዲያ ሊኖረን ይገባል። አለበለዚያ ግን፤ እስከዛሬ የምናውቀው የግሉፕሬስ ማህበረሰብ መሰረታዊ ችግር ወልዶ ባሳደገው ጽንፈኛ አስተሳሰብ መባባስ ምክንያት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢነቱ እየጨመረ ሲመጣ የሚስተዋለው ጸረ ዴሞክራሲ አመለካከት ባለበት ሁኔታ ውስጥ የሚዳክር ጋዜጠኛ ተይዞ የመገናኛ ብዙኃን ሙያ ዘርፉን ቁመና የህዳሴው ዘመን ኢትዮጵያዊነት በሚጠይቀው ልክ ኃላፊነት የሚሰማው ማድረግ ይቻላል ብሎ ማመን ያዳግታል።

በሌላ አነጋገር፤ ለማይቀለበስ የሕግ የበላይነት መረጋገጥ ዘብ ከመቆምና ለጤናማ የፖለቲካ ኃይሎች ሰላማዊ ትግል ተጠናክሮ መቀጠል በትጋት የመስራትን ዴሞክራሲያዊ መርህ ሳያዛንፍ መተግበር እንዳለበት የሚያምን ጠንካራ የሚዲያ ተቋም በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲኖረን የኢትዮጵያ የህዳሴ ጉዞ ዳር የማድረስ ተስፋችንም አስተማማኝ ይሆናል። ስለዚህም የኢፌድሪ መንግስት አሁን ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ስለመሆኑ የሚነገርለትን የሚዲያ መዋቅራዊ ማሻሻያ (ሪፎርም) ከመርህ የለሽነት ችግር ተላቆ፤ የኢትዮጵያን የህዳሴ ጉዞ የማስቀጠልና ብሎም ዳር የማድረስ ታሪካዊ ተልዕኮውን በአግባቡ መወጣት እንደሚጠበቅበት ከልቡ የሚያምን የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያ ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ የተቃኘ መሆን ይኖርበታል።

ዘርፉ ከላይ የተመለከቱትን ቁልፍ ሀገራዊ አጀንዳዎች ደረጃ በደረጃ እያሳካን የኢትዮጵያን ፈርጀ ብዙ የህዳሴ ጉዞ ወደ ፊት ለማስቀጠል የምናደርገውን ያላሰለሰ ጥረት የመወሰን ሚና ያለው እንደመሆኑ መጠን፤ በተለይም ከለየለት የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት ጽንፈኛ አስተሳሰብ መጽዳት ይኖርበታል

ተብሎ ይታመንናል። በአጠቃላይ በዛሬዋ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ያለበት የሚዲያ ተቋም፤ መላው የሀገራችን ህዝቦች ለዘላቂ ዕጣ ፈንታቸው መቃናት ጽኑ መሰረት የጣሉበትን የኢትዮጵያ ህዳሴ ጉዞ ከቅልበሳ አደጋ የመታደግ ሙያዊና ታሪካዊ ኃላፊነት የሚሰማቸው ተራማጅ ጋዜጠኞች በንቃትና በብቃት የሚንቀሳቀሱበት ህዝባዊ የመገናኛ ብዙኃን ዘርፍ ነው እንጂ፤ ከቶውንም አደጋ የሚጋብዝ መሆን የለበትም የሚለው ነጥብ ላይ ሊሰመርበት ይገባል እላለሁ።